

# Entrepreneur SPARK

Vol.I No.1, September 2015

*A quarterly newsletter of the Entrepreneurship Development Center*

**Entrepreneurship Development Centre (EDC) - Ethiopia**

የኢንተርፕሩነርሽፕ ልማት ማዕከል-ኢትዮጵያ

## Message from the CEO



Dear Readers,

I'm very happy to share with all of you the first issue of our quarterly newsletter which will go a long way towards documenting our good practices, news and success stories around unleashing the entrepreneurial energies of Ethiopians.

The Entrepreneurship Development Centre - Ethiopia (EDC-Ethiopia) was established in May 2013 to oversee the successful implementation of the Entrepreneurship Development Programme (EDP), launched by H.E. Prime Minister Hailemariam Desalegn in February of the same year.

Our center is a semi-autonomous entity that works under the auspices of the Ministry of Urban Development, Housing, and Construction (MoUDHCo) and the Federal Micro and Small Enterprise Agency (FeMSEDA). We provide innovative entrepreneurship skills training and customized business development services to new and existing micro, small and medium enterprises in Ethiopia.

Since our establishment, we have worked hard to help accelerate transformational and sustainable development through tapping into the creativity and ambition of existing and aspiring Ethiopian entrepreneurs.

We do this through identifying growth-oriented enterprises as well as potential entrepreneurs, targeting unemployed youth and women nationwide, and providing them with direct support to enhance their entrepreneurial skills and competencies.

In the past two years, we have provided business support services to over 5000 start-ups and existing businesses. Over 23,000 Ethiopians across the country have taken entrepreneurship training. Customized training for women and youth has also been successfully organized to meet the specific needs of this hugely untapped group.

## In This Issue:


- *UNSG visits entrepreneurship intervention for women and female youth*
- *Scaling up Business Development Services*
- *Thousands of Trainees Benefit from Entrepreneurship Training*
- *Young entreprenurs trained on Microsoft's Build Your Business*
- *Entrepreneurship Trainers Certified by UNCTAD*
- *Widening the pool of Business Development Services Advisors*
- *INSIHD Ethiopia chapter launched*
- *Intrapreneurship training targets senior government officails*
- *Awarding outstanding Ethiopian Entrepreneurs*
- *Supporting innovation*
- *Sensitization training on Gender and Entrepreneurship*
- *Events update*


*In February 2013 His Excellency Prime Minister Hailemariam Desalegn officially launched the Entrepreneurship Development Programme (EDP) developed by UNDP in partnership with the Ministry of Urban Development and Construction to foster the emergence of a robust and entrepreneurial MSME sector. The EDP is implemented on the ground by the Entrepreneurship Development Centre and the Federal Micro and Small Enterprises Development Agency (FeMSEDA).*

EDC has also partnered with public universities to establish centers of excellence for entrepreneurship in order to help graduating students become job creators rather than joining the growing number of job seekers in the country. Currently available statistics places urban youth unemployment rate at 22.8% while that for urban female youth stands at 28.8%.

The centers are being set up in Addis Ababa University, Adama Science and Technology University, Hawassa University, Bahir Dar University and Mekelle University.

We have also partnered with the Education Strategic Center set up by the Ministry of Education in order to enhance entrepreneurship curriculum into higher education and review researches that will act as an input for policy formulation.

In order to effectively expand our service throughout the country, EDC-Ethiopia opened regional offices in 2014 in the towns of Bahir Dar, Mekelle, Hawassa and Bishoftu.

Let me take this opportunity to warmly acknowledge the invaluable support that the Entrepreneurship Development Centre has received from UNDP to effectively succeed in our work. The Government of Canada has been a key supporter of the entrepreneurship development programme, with a particular focus on women and female youth. Our partnership with the First Lady's Office and CAWEE is also helping to push the women's empowerment agenda along. This partnership was commended by UN Secretary General Ban Ki-moon during his site visit to the women's traditional handicraft workshop when he was in Addis in late July 2015 for the third Financing for Development Conference.

Our partnership with EMPRETEC-Ghana Foundation, Microsoft East Africa LTD and UNCTAD is also helping to strengthen the delivery of our services to our clients – the Ethiopian entrepreneurs.

I would like to cordially invite our clients and partners to contribute their news, updates and success stories around entrepreneurship so that we work together to make this newsletter an interactive knowledge sharing platform.

Happy reading!

Etalem Engeda

Chief Executive Officer,

EDC-Ethiopia

## UNSG Visits Entrepreneurship Intervention for Women and Female Youth

United Nations Secretary General Ban Ki-moon visited a UNDP supported entrepreneurship development project that trains and equips Ethiopian women and female youth from vulnerable backgrounds to access the export market. The secretary general was accompanied by his Special Adviser on Post-2015 Development Planning, Ms. Amina Mohammed.

The women work in traditional hand-weaving, spinning, embroidery, crotchet, and hand-knitting, as well as basketry, gemstone jewelry and leather.

Prior to joining this project, the women, mostly engaged in collecting and selling fire-wood, earned on average a monthly income of less than US$20; their income has now on average increased four-fold and is expected to grow further as they hone their skills and expand their access to markets.

Single mother of three, Aselefech Abebe is one of the women who is now benefiting from this project. Aselefech is a former soldier who fled to Sudan and lived there as a refugee for five years following the change in government back in 1991. Upon her return to Ethiopia she married a weaver and had three daughters. When her husband suddenly passed away, Aselefech found herself without any skills to enable her to make a good living for her young family. Now that she has joined the project, Aselefech is earning more and able to take care better care of her family.



UN Secretary General Bank Ki-moon with Ethiopian First Lady Roman Tesfaye with female weaver. UN Photo/Eskinder Debebe

Ethiopia's First Lady Roman Tesfaye was also on hand to join the UN Secretary General for the site tour of the project, which was launched by her office back in February 2014 in partnership with the Center for Accelerated Women Economic Empowerment (CAWEE) and the Entrepreneurship DevelopmentCentre- Ethiopia to target 1,500 women and female youth.

Speaking at the launch of the project, Ambassador David Usher of Canada, had underlined the importance of unleashing the potential of women entrepreneurs, noting that "Access to information and markets are the biggest challenges for many of the female entrepreneurs".

Canada is a key partner of the Entrepreneurship Development Programme (EDP), and has provided 5.8 million USD to the programme to help build the entrepreneurial capacity of around twenty-five thousand Ethiopian women and youth.

## Scaling up Business Development Services

EDC has signed a memorandum of understanding with a Netherlands-based NGO CORDAID and R&D Entrepreneurship and Outsourcing Centre PLC to provide business development service support for medium enterprises in Ethiopia. An experts' seminar and networking session was held on 21st August 2015. The seminar provided participants with ideas on professionalism and innovative solutions for their businesses.

## Thousand of Trainees Benefit from Entreprenurship Training Workshops

The 218th Entrepreneurship Training Workshop (ETW) was held in Addis Ababa from 27 July – 1 August 2015. Over 23,000 established and aspiring entrepreneurs across the country have so far taken part in the EDC Entrepreneurship Trainings from all over the country.



Some of the participants of the 218th ETW Session during the group work exercises

The 200th session of ETW took place in Mekelle July 2015. The special milestone event was attended by Ato Asmelash Bezabeh, Deputy Director General of FeMSEDA and Ato Tilahun Tarekegn, Director General, Tigray

Regional State Enterprises Development Agency.

## Young Entrepreneurs Trained on Microsoft's Build your Business

Two hundred young men and women entrepreneurs took part in the first Build Your Business (BYB) training session held in the bustling cities of Bahir Dar and Hawassa in June 2015.

The BYB training seeks to develop the knowledge and skills of those looking to sustain existing businesses as well as those wishing to start a new micro and small enterprise.

The training is part of UNDP's partnership with Microsoft East Africa around the Entrepreneurship Development Programme (EDP).

Most of the trainees are already benefiting from the EDP's Business Development Services provided by the Entrepreneurship Development Center (EDC).

## Entrepreneurship Trainers Certified by UNCTAD

Twenty local entrepreneurship trainers who have been facilitating entrepreneurship training workshops for more than a year have been certified by UNCTAD as national entrepreneurship trainers. The trainers are business owners as well as lecturers from Addis Ababa, Haswassa, Mekelle, Bahir Dar, Haramaya, and Wollega universities.

The two five - day intensive evaluation and certification sessions for local trainers equipped participants with innovative and cutting edge skills in providing entrepreneurship trainings. The trainers were also exposed to international experience so that they would eventually become International Master Trainers for Entrepreneurship.



Local trainers certified by UNCTAD as national entrepreneurship trainers

# Widening the Pool of Business Development Services Advisors

The tenth business development services advisors' training session has been held successfully, adding 52 trained advisors to the national pool, which now stands at 226.

BDS advisors have provided coaching and mentorship to over 5,000 entrepreneurs throughout the country to help them establish and grow their businesses.

Business Development Service Advisors are assigned to clients who have completed the entrepreneurship training workshop and who are in need of customized business development support. The advisor and the client agree upon intervention strategies and meet regularly for a period of 6 to 9 months.



10th BDS Advisors' training participants receive certificates

# International Network of Social Innovators for Human Development (INSHID) Ethiopia Chapter Launched

The INSIHD Ethiopia Chapter was launched on April 23, 2015 at the Hilton Addis Ababa Hotel in the presence of H.E. Getachew Negash, State Minister, Ministry of Communication and Information Technology.

The Chapter acts as a forum to bring together social innovators and policy makers to tackle pressing development priorities.

INSIHD is a result of a partnership between UNDP and Motorola Solutions aimed at supporting social innovators and development practitioners in deploying and using mobile technologies for fostering human development.

INSIHD meetings in Nairobi, Tunis, Kigali, Berlin, Dakar, and Addis Ababa has helped to foster the creation of national INSIHD chapters.




INSIHD Ethiopia Chapter Launch

# Intrapreneurship Training Targets Senior Government Officals

Senior officials and experts from the Federal and Regional Micro and Small Enterprises Agencies (FeMSEDA and ReMSEDA) have taken part in a five day customized workshop on intrapreneurship in Addis Ababa to introduce them to the art of thinking like the entrepreneurs whom they support in their day to day engagements.

FeMSEDA and ReMSEDA are responsible for creating numerous jobs and help increase the income of Ethiopia's workforce by creating a reliable, broad based competitive sector for industrial development.

# Awarding Outstanding Ethiopian Entrepreneurs

EDC took the opportunity of the 2015 UNDP Entrepreneurship award, held in March 2015, to introduce the annual EDC Entrepreneur of the Year award.

The award celebrates the success of entrepreneurs who have taken the entrepreneurship training and accessed BDS.

The 2015 UNDP Entrepreneurship Award recognized entrepreneurs in six categories: Entrepreneur of the year, Environmental Sustainability Entrepreneur, Small and Medium Enterprise (SME) Entrepreneur, Young Female- Entrepreneur, Young Male entrepreneur, Rural Entrepreneur.

The award recognized outstanding entrepreneurs based on their work's impact on the community, contribution to creating new jobs and their sustainability.

Speaking at the occasion, the guest of honour, H.E. Prime Minister Hailemariam Desalegn said, "Our government has given emphasis to develop micro and small enterprises as they are the most viable means to create new employment opportunities and stimulate economic growth."



H.E. Mr. HaileMariam Dessalegn and UNDP Ethiopia Resident Representative Mr. Eugene Owusu handing over the prize for the Entrepreneur of the Year. The winner of the USD 20, 000 cash prize sponsored by UNDP was Ato Kebede Lakew who runs a climate friendly business introducing local organic fertilisers to the Ethiopian agriculture sector



UNDP Ethiopia Goodwill Ambassador for Entrepreneurship Ms. Bethlehem Tilahun, founder and manager of the eco-friendly SoleRebels shoe company, handing over the check for the Young Female Entrepreneur of the Year award winner. The USD 10,000 cash prize was co-sponsored by UNDP and SoleRebels.




UNDP Resident Representative Mr Eugene Owusu with two of the EDC's Business Development Service Advisors.

Partnering UNDP to recognize these entrepreneurs by providing financial support for the winners were:

SoleRebels which co-sponsored the USD 10,000.00 Young Female Entrepreneur award; Tivoli Trading PLC, which sponsored the USD 5,000.00 EDC Start Up award; Foundation Green Ethiopia and Yesera Betachin joined to co-sponsor the USD 5,000.00 Environmental Sustainability award; while Enat Bank and Bunna-International Bank co-sponsored the USD 5,000.00 Rural Entrepreneur award. Kenya Airways provided return economy tickets to the runners up of the Entrepreneur of the Year Award.

The call for applications for the 2016 entrepreneurship award is expected to be announced soon and interested entrepreneurs are encouraged to follow up on www.et.undp.org for more news as well as videos featuring the 2015 award winners.

## Supporting Innovation

EDC Ethiopia has opened an Innovation Service Centre within its Addis Ababa office premises. This development was announced during the 6th Innovation Breakfast Meeting held in March 2015 in the presence of stakeholders including the director of the Ethiopian Intellectual Property Rights Office, government officials, and members of the private sector, academia, and NGOs.

The innovation centre provides a platform for innovators and entrepreneurs to share their experiences, exchange ideas, build networks, enhance their innovation capacity, and commercialize their inventions and innovative ideas.

EDC has also provided entrepreneurship training for the top 40 innovators selected from a nationwide competition run by the Ministry of Urban Development, Housing and Construction.

## Sensitisation Training on Gender and Entreprenurship Runs

EDC's Gender and Business Officer, Sewit Haileselassie, organised a gender sensitization training for EDC staff, business development service advisors, and entrepreneurship trainers in April 2015. The training is expected to help mainstream gender into the work of the EDC more effectively.

Similar trainings have taken place in Mekele in July for BDS advisors and trainers. Centre of Excellence for Entrepreneurship coordinators (COEE) in Bahir Dar and Hawassa Universities also had a chance to take part in the training.

# Events Update

## Entrepreneurship Training Workshop (ETW):

The 226th session of the ETW was held from 17-22 August 2015 in Addis Ababa. Six ETW sessions were held during the same week in Wolisso, Hawassa, Gonder, Woldia Mekelle and Dembi-Dollo towns.

The ETW is an intensive six-day training aimed at helping entrepreneurs to put their idea into action, induce successful entrepreneurial attitudes and build their personal entrepreneurial skills.

## Customised Entrepreneurship Training:

Three Customised Trainings have been held from 17 – 22 July 2015 in Wolisso, Woldia and Dembi-Dollo towns.

The customised two-day training target women and youth entrepreneurs who have limited business literacy. Over 5,400 trainees have so far benefited from this customized training programmes.

## Training of Business Development Service Advisors:

The BDS Advisors training will be held in September 2015 in Addis Ababa

Those wishing to become BDS advisors can look forward to ten-day training focusing on the provision of services on a one-to-one bases. The training includes an in-class sessions that lasts for five days, which is then followed up by on-site practice for the next five days. To date, seven sessions of such trainings for potential advisors have been organized for potential advisors selected from among ETW graduates.

## Innovation for Development Breakfast Meetings:

The breakfast meeting is scheduled for late September 2015

EDC has collaborated with UNDP to conduct six innovation for development breakfast meetings so far bringing together innovators and entrepreneurs who are clients of the EDC's BDS.

The meetings provide a platform for social innovators, entrepreneurs, academia, and partners from public, private, civil society sectors to exchange ideas, build networks and discuss how the power of innovation can be harnessed for development in Ethiopia.

# ENTREPRENEURSHIP DEVELOPMENT CENTER (EDC)-ETHIOPIA

*In February 2013 His Excellency Prime Minister Hailemariam Desalegn officially launched the Entrepreneurship Development Programme (EDP) developed by UNDP in partnership with the Ministry of Urban Development and Construction to foster the emergence of a robust and entrepreneurial MSME sector. The EDP is implemented on the ground by the Entrepreneurship Development Centre and the Federal Micro and Small Enterprises Development Agency (FeMSEDA).*

*Government of Canada and Microsoft East Africa have come on board to partner on the EDP.*

Nega city building Kazanchis Addis Ababa, Ethiopia
**Office number:** +251 115 571 164/8 **Fax:**+251 115 571 208
**www.edcethiopia.org**
E-mail: edc.center@undp.org
Facebook: edcethiopia12

# የኢትዮጵያ የኢንተርፕረነርሺፕ ማዕከል

ነጋ ሲቲ ህንጻ፣ ካዛንቺስ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
የቢሮ ቁጥር: +251 115 571 164/8 ፋክስ: +251 115 571 208

ዌብሳይት: www.edcethiopia.org

ኢ-ሜይል: edc.center@undp.org
Facebook: edcethiopia12



እ.አ.አ በየካቲት ወር 2013 ጠ/ሚር ሃ/ማርያም ደሳለኝ በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) እና በከተማ ቤቶችና ልማት ኮንስትራክሽን በጋራ የተጀመረውን የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ፕሮግራም መርቀው ከፍተዋል፡፡ ይህም ፕሮግራም በኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ማዕከል ኢትዮጵያ (EDC) እና በፌዴራል አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ ይተገበራል።

በተጨማሪም የካናዳ መንግስት እና ኢስት አፍሪቃ ማይክሮሶፍት ካምፓኒ ፕሮግራሙን እየደገፉ ይገኛሉ።

# የመንግስት ከፍተኛ ሀላፊዎች ኢንተራፐረነርሽፕ ስልጠና ወሰዱ

የፌዴራልና የክልል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች ልማት ኤጀንሲ ከፍተኛ ሀላፊዎችና ባለሙያዎችን ትኩረት ያደረገ የአምስት ቀናት ወርክሾፕ በአዲስ አበባ ተካሂዷል፡፡

በወርክሾፑ በተገኘው ስልጠና ሀላፊዎቹ እለት በእለት ድጋፍ የሚሰጧቸው የስራ ፈጣሪዎች የኢንተርፕረነር አስተሳሰብ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡

የፌዴራልና የክልል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፐራይዞች ልማት ኤጀንሲዎች በርካታ ስራዎች እንዲፈጠሩ፣ የኢትዮጵያውያን ገቢ እንዲያድግ ከመስራታቸውም ባሻገር ለኢንዱስትሪ ልማቱ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ተወዳዳሪና መሰረት ያላቸው የስራ ዘርፎችን በመፍጠር ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡

# የፈጠራ ግኝት ማዕከል ተቋቋመ

የኢንተርፕረነርሽፕ ልማት ማዕከል በአዲስ አበባ በሚገኘው የማዕከሉ ቢሮ የፈጠራ ግኝት አገልግሎት ማዕከል ከፍቷል፡፡ ማዕከሉ በ6ተኛው ዙር የፈጠራ ግኝት ስብሰባ ላይ አገልግሎት መስጠት መጀመሩ የተገለፀ ሲሆን በዚህ ስብሰባ ላይ የኢትዮጵያ አዕምሮአዊ ንብረት ኤጀንሲ ዳይሬክተር፣ ከፍተኛ የመንግስት የሥራ ኃላፊዎች፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና የግል ዘርፉ ተወካዮች ተገኝተዋል፡፡

ይህ ማዕከል ስራ ፈጣሪዎች እና ኢንተርፐረነሮች ሃሳብ እንዲለዋወጡ፣ ግንኙነት እንዲፈጥሩ፣ የስራ ፈጠራ ክህሎታቸውን እንዲያሻሻሉ እና የፈጠራ ውጤቶቻቸውን ለገበያ እንዲያቀርቡ የሚረዳቸው እንደሆነ ታምኖበታል፡፡

# በስርዓተ ጾታ ላይ ያተኮረ ስልጠና ተካሄደ

የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ማዕከል ሰራተኞች፣ አማካሪዎች እና ኢንተርፕረነርሺፕ አሰልጣኞች የስርዓተ-ፆታ ስልጠና ወስደዋል።

ስልጠናው ሚያዚያ ወር 2007 ዓ.ም ኢጋማሽ ላይ በኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ማዕከል የስርዓተ ጾታ ቢዝነስ ኃላፊ ወ/ሮ ሰዊት ሀ/ስላሴ የተሰጠ ሲሆን ስርዓተ-ፆታን በማዕከሉ አሰራር ውስጥ በጠነከረ ሁኔታ ለማስረፅ ይረዳል።

ተመሳሳይ ስልጠናዎች በመቀሌ ለቢዝነስ ልማት አገልግሎት አማካሪዎች እና አሰልጣኞች በሐምሌ ወር ተሰጥቷል። በዚህ ስልጠና ላይ የባህር ዳር እና ሃዋሳ ዩኒቨርስቲ የኢንተርፕረነርሺፕ ክህሎት ማዕከል አስተባባሪዎች ተሳትፈዋል።

# ቀጣይ ክንውኖች

የኢንተርፕረነርሺፕ ስልጠና ወርክሾፕ/ETW/

226 ኛው የኢንተርፕረነርሺፕ ስልጠና ከነሐሴ 11-16/2007 ዓ.ም በአዲስ አበባ ተካሄደ ፡፡ የስድስት ቀን ስልጠናው በተመሳሳይ በወሊሶ፣ ሀዋሳ፣ በጎንደር፣ ወልዲያ፣ መቀሌ፣ እና ደንቢ ዶሎ ከተማ ተካሂዷል ፡፡ ስልጠናው ውጤታማ የሆነ የኢንተርፕረነር አስተሳሰብ እንዲፈጥሩ እገዛ ያደርጋል ፣ የግል ኢንተርፕረነርሺፕ ክህሎታቸውንም እንዲያዳብሩ ይረዳል ፡፡

የኢንተርፕረነርሺፕ ማሻሻያ ስልጠና

ሦስት የኢንተርፕረነርሺፕ ማሻሻያ ስልጠናዎች ከሐምሌ 10-15/2007 ዓ.ም በወሊሶ፣ በወልዲያ እና ደንቢ ዶሎ ከተማ ተካሂዷል ፡፡ ስልጠናው ሴቶችና ወጣቶችን ማዕከል አድርጎ ስራ ፈጣሪዎችን በቢዝነስ ላይ ያለባቸውን ውስንነት ለማሻሻል የሚሰጥ ስልጠና ነው ፡፡ በስልጠናው የእስካሁን እንቅስቃሴም ከ 5400 በላይ ስራ ፈጣሪዎች ስልጠና አግኝተዋል ፡፡

የቢዝነስ ልማት አገልግሎት አማካሪዎች ስልጠና

(መስከረምና ጥቅምት 2008)

የቢዝነስ ልማት አገልግሎት አማካሪዎቹ ከደንበኞቻቸው ጋር አንድ ለ አንድ በሚያደርጉት ግንኙነት የሚጠቅማቸው ስልጠና ነው፡፡ለ10 ቀናት የሚካሄደው ስልጠና በመጀመሪያዎቹ አምስት ቀናት የክፍል ውስጥ በቀጣዮቹ አምስት ቀናት ደግሞ የተግባር ስልጠና ይሠጥበታል።

ከኢንተርፕረነርሺፕ ስልጠና ወርክሾፕ የተገኙ ጠንካራ አማካሪዎችን አቅም ለማሳደግ ይረዳል ፡፡ ስልጠናው ከዚህ በፊት ለ10 ጊዜያት ተካሂዷል፡፡

የአዲስ ፈጠራ ልማት ማነቃቂያ ስብሰባ

(የማነቃቂያ ስብሰባው በመስከረም ወር 2008 ዓ.ም ይካሄዳል)

የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ማዕከል ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ልማት ፕሮግራም ጋር በመተባበር ስድስት የአዲስ ፈጠራ ልማት ማነቃቂያ ስብሰባዎችን አድርጓል ፡፡ ማነቃቂያ ስብሰባው የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ማዕከል ደንበኞችን አብሮነት እና ትስስር የሚፈጥር ነው ፡፡

ማነቃቂያው የአዳዲስ ግኝት ባለቤቶች ከህዝባዊና የግል ተቋማት እንዲሁም ሲቪል ማህበራት ጋር ልምዳቸውን እንዲያጋሩ ፤ ሃሳብ እንዲለዋወጡ ፤ ትስስር እንዲፈጥሩ የፈጠራ አቅማቸውን እንዲያሳድጉና የፈጠራ ግኝት ሃሳባቸውን ወደ ገበያ እንዲቀይሩ ሰፊ መደላድል ይፈጥራላቸዋል ፡፡

# የዓለም ዓቀፍ ኔትወርክ የማህበራዊ ግንኙነት ትብብር (INSHID) የኢትዮጵያ ቅርንጫፍ በይፋ ተከፈተ

ዓለም ዓቀፍ ኔትወርክ የማህበራዊ ግንኙነት ትብብር የኢትዮጵያ ቅርንጫፍ የኮሙኒኬሽን ሚኒስትር ዴኤታ ክቡር አቶ ጌታቸው ነጋሽ በተገኙበት ሚያዚያ 16 ቀን 2007 ዓ.ም በአ.አ በይፋ ተከፍቷል ፡፡

ዓለም ዓቀፍ ትብብር ኔትወርክ በፎረም መልክ የተቋቋመ ሲሆን የአዲስ የፈጠራ ባለሙያዎች ከፖሊሲ አውጪዎች ጋር በጋራ እንዲሰሩ የሚያደርግ ነው ፡፡

INSHID የተመሰረተው በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም እና በሞቶሮላ ሶሉሽንስ ሲሆን የተንቀሳቃሽ ቴክኖሎጂ በመጠቀም አዳዲስ የፈጠራ ውጤቶችን ለማህበራዊ ልማት ትብብር ግብዓት የሚሆንበትን አሰራር ለመፍጠር ነው፡፡

የዓለም አቀፍ ትብብር ኔትወርክ ስብሰባዎች ከዚህ ቀደም በኖይሮቢ፣ በቱኒዝ፣ ኪጋሊ፣ በርሊን፣ ዳካር እና አዲስ አበባ ከተሞች የተካሄደ ሲሆን ትብብሩ አህጉራዊ ቅርንጫፍ ለመመስረት የሚያስችል ነው፡፡




ኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ማዕከል የአዲስ ግኝት አገልግሎት ማዕከል ከፈተ

# የላቁ ኢትየጵያውያን ኢንተርፕረነሮች ሽልማት ተሰጣቸው

የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) ኢትዮጵያ የ2015 የኢንተርፕረነሮች ውድድር ሽልማት የካቲት 30 ቀን 2007 ዓ.ም በሸራተን አዲስ በተካሄደ ስነስርዓት ላይ ተከናውኗል።

በሽልማት ስነ-ስርዓቱ ላይ የተገኙት ጠ/ሚር ሃ/ማርያም ደሳለኝ የመክፈቻ ንግግር ያደረጉ ሲሆን "የኢትዮጵያ መንግስት ለአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች መስፋፋት የሰጠው ትኩረት ለስራ ፈጠራ እና ለኢኮኖሚ እድገት እንደመነሻ ግብዓት ሆኗል" ብለዋል ፡፡

በ2007 ዓ.ም የፈጠራ ስራ ሽልማቱ በስድስት ዘርፎች ለተወዳደሩ ኢንተርፕረነሮች የተሰጠ ሲሆን ዘርፎቹም የዓመቱ ተመራጭ

ኢንተርፕረነር፤ በተፈጥሮ ጥበቃና እንክብካቤ ፤ በአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ፤ በገጠር ልማት ለተከናወኑ ስራዎች፣ በወጣት ሴት እና ወንድ ኢንተርፕረነሮች፤ በተጨማሪም የ(EDC) ለጀማሪ ኢንተርፕረነር የተደረገ ሽልማት ነው።




በሸራተን አዲስ በተዘጋጀው የሽልማት ስነ-ስርዓት ላይ ጠ/ሚር ሃ/ማርያም ደሳለኝ ነዋሪነታቸው በኢትየጵያ ከሆኑት ሚ/ር ዩጂን አውሱ ጋር በመሆን ሽልማት የሰጡ ሲሆን የ20 ሺህ የአሜሪካን ዶላር ሽልማት ስፖንሰር የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ነው ፡፡



የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም የኢንተርፕረነርሺፕ የክብር አምባሳደር እና የሶል ሬብልስ መስራችና ሥራአስኪያጅ ቤተልሄም ጥላሁን በድርጅታቸው እና በመንግስታቱ ድርጅት የልማት ፕሮግራም ስፖንሰር የተደረገውን የዓመቱ የወጣት ሴቶች የኢንተርፕረነርሺፕ ተሸላሚ ለሆኑት የ10 ሺህ ዶላር ሽልማት ሲያበረክቱ




መሀል ሚ/ር ዩጂን አውሱ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የኢትዮጵያ አስተባባሪ

# የኢንተርፕረነርሺፕ ስልጠና ሺዎች ተጠቃሚ እያደረገ ነው

የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ማዕከል (EDC) የሚሰጠው የስራ ፈጠራ ስልጠና ከመላው ሀገሪቱ የተውጣጡ 23 ሽህ በላይ ሰልጣኞችን ተጠቃሚ አደረገ ፡፡ የ218ኛ የኢንተርፕረነርሺፕ ወርክሾፕ (ETW) በአዲስ አበባ ከሐምሌ 20-25 ቀን 2007 ዓ.ም ተደርጓል ፡፡




የ 218ኛ ኢንተርፕረነርሺፕ ሰልጣኞች በከፊል

# ወጣት የስራ ፈጣሪዎች የራስ ቢዝነስ ግንባታ (BYB) ስልጠና አገኙ

ወጣት ወንድ እና ሴት ኢንተርፕረነሮች የራሳቸውን ቢዝነስ ለመገንባት የሚያስችል ዓላማ ያለው ስልጠና ተሰጣቸው። ስልጠናው እውቀታቸውን እና ክህሎታቸውን ተጠቅመው በአነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞች በመደራጀት ዘላቂና ቀጣይነት ያለው ቢዝነስ መስራት የሚችሉበት ስልጠና ነው ፡፡

ስልጠናው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም (UNDP) አካል ሆኖ ከኢስት አፍሪቃ ማይክሮሶፍት ካምፓኒ እና ከኢንተርፕረነርሺፕ የልማት ፕሮግራም (EDC) ጋር በትብብር የተከናወነ ነው ፡፡ የካናዳ መንግስት ዋነኛው የኢንተርፕረነርሺፕ የልማት ፕሮግራም አጋዥ ሲሆን 5.8 የአሜሪካ ዶላር የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል ፡፡ በዚህ ስልጠና ከ28 ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን ሴት እና ወንድ ወጣት የስራ ፈጠራ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡

የመጀመሪያዎቹ 200 የዚህ ፕሮግራም ስልጠኞች ከባህር ዳር፣ እና ከሀዋሳ የተውጣጡ ሲሆን ስልጠናውም በሰኔ ወር 2007 ዓ.ም ተካሂዷል ፡፡ አብዛኛዎቹ የዚህ ፕሮግራም ሰልጠኞች ኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ማዕከል (EDC)ከ ኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ፕሮግራም (EDP) ጋር በመተባበር ባዘጋጀው ስልጠና መጠቀማቸውን ገልጸዋል ፡፡

# የኢንተርፕረነርሺፕ አሰልጣኞች በተባበሩት መንግስታት የንግድና የልማት ድርጅት እውቅና አገኙ

ከአንድ ዓመት በላይ በኢምፐርቴክ የአሰለጣጠን ዘዴ የሰለጠኑ 20 የሚሆኑ ከሀገር ውስጥ የተውጣጡ የኢንተርፕረነርሺፕ አሰልጣኞች በተባበሩት መንግስታት የንግድና የልማት ድርጅት እውቅና አግኝተዋል ፡፡ ሰልጠኞቹ ከአዲስ አበባ ፣ ከሀዋሳ፣ መቀሌ፣ ባህርዳር ፣ ሃረማያ እና ወሊጋ ዩኒቨርሲቲ የተውጣጡ ናቸው ፡፡

የዕውቅና ስልጠናው የተሳታፊዎቹን የኢንተርፕረነርሺፕ ክህሎት እና እውቀት እንዲያዳብሩ አስችሏቸዋል፡፡በተጨማሪም ሰልጣኞቹ የዓለም ዓቀፍ ተሞክሮ እንዲያገኙ የተደረገ ሲሆን ለወደፊቱ ዓለም ዓቀፍ አሰልጣኞች እንዲሆኑ የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡



በተባበሩት መንግስታት የንግድና የልማት ኮንፈረንስ እውቅና ያገኙ አሰልጣኞች

# የቢዝነስ ልማት አገልግሎት አማካሪዎች ቁጥር አደገ

10ኛ ዙር የቢዝነስ ልማት አገልግሎት የአማካሪዎች ስልጠና ተሰጠ። በስልጠናው 52 የሚሆኑ አዲስ አማካሪዎች ስልጠና ያገኙ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ማዕከል ስልጠና ያገኙ የአማካሪዎች ብዛት ወደ 226 አድርሶታል።

በማዕከሉ የሚገኙ አማካሪዎች እስከዛሬ ከ5000 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ከመላው ሀገሪቱ ለተውጣጡ ኢንተርፕረነሮች የቢዝነስ አቅማቸውን እንዲያሳድጉ ከፍተኛ እገዛ አድርጓል።

እነዚህ የቢዝነስ ልማት አገልግሎት አማካሪዎች ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ለእያንዳንዱ ኢንተርፕረነር ሰልጣኝ የሚመደቡ ናቸው። አማካሪዎቹና ሰልጣኞች በየጊዜው እየተገናኙ ስለቢዝነሳቸው ምክር የሚሰጣቸው ሲሆን ለጀማሪዎች 9 ወር ለ ነባር ቢዝነሶች 6 ወር የሚደርስ የማማከር አገልግሎት በልማት ማዕከሉ አማካሪዎች ይሰጣል፡፡



የ10ኛ ዙር የቢዝለስ ልማት ተሳታፊዎች የሰርተፊኬት ሽልማት

ይህንን የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ማዕከል ከጥንስሱ ጀምሮ በመደገፍና በመርዳት የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) ከፍተኛ አስተዋፅኦ እያደረገ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የካናዳ መንግስት ማዕከሉን በግንባር ቀደምትነት የሚደግፍ ሲሆን በተለይም ትኩረቱ ወጣቶችና ሴቶችን ያማከለ ነዉ፡፡

እንዲሁም ማዕከሉ ከቀዳማዊት እመቤት ቢሮ እና ከሴንተር ፎር አክስለሬቲንግ ውመን ኢኮኖሚክ ኢምፓወርመንት (CAWEE) ጋር እየሰራ ይገኛል፡፡ ይኸውም የጋራ ስራ የሴቶች የባህላዊ ዕደ ጥበብ ማዕከል ሲሆን ይሄንንም በቅርቡ በአዲስ አበባ በተካሄደው ፋይናንሲንግ ፎር ዲቨሎፕመንት (FFD) ጉባኤ ላይ የተገኙት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ባንኪሙን ጎብኝተውት አድናቆታቸውን ገልፀውልናል፡፡

ከኢምፐርቴክ- ጋና ፋውንዴሽን ፣ ከኢስት አፍሪቃ ማይክሮሶፍት ካምፓኒ እና የተባበሩት መንግስታት የንግድ እና ልማት ድርጅት ጋር ያለን የስራ ትስስር ለማዕከሉ ስራ መቃናት ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ በላይ ለጠቀስኳቸው አጋሮቻችን በራሴና በማዕከሉ ስም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም የማዕከላችን ደንበኞች እና አጋሮቻችን በዚህ ዜና መጽሔት የሚወጡትን ዜናዎች እና መልካም ተሞክሮዎቻችሁን በማካፈል የዜና መጽሔቷ ደንበኞች እንድትሆኑ በአክብሮት እጋብዛለሁ። አመስግናለሁ።

መልካም ንባብ!

**እታለም እንግዳ**

የኢንተርፕረነርሺፕ የልማት ማዕከል(ኢትዮጵያ)

ዋና ሥራ አስፈጻሚ



የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ ባንኪሙን ከቀዳማዊት እመቤት ወ/ሮ ሮማን ተስፋዬ ጋር ፕሮጀክቱን በጎበኙበት ወቅት (ፎቶ በእስክንድር ደበበ)

## የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ የሴቶችን የኢንተርፕረነርሺፕ ፕሮጀክት ጎበኙ

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ባንኪሙን በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም የሚደገፈውን የሴቶች የኢንተርፕረነርሺፕ ፕሮጄክት ጎበኙ ፡፡ ፕሮጄክቱ ሴቶችን በተለይም ደግሞ ወጣት ሴቶችን በማደራጀት ቀድሞ በባህላዊ መንገድ ሲሰሯቸው የነበሩትን የእጅ ስራ ወጤቶች ተወዳዳሪነታቸው እንዲጨምርና የገበያ ትስስር እንዲኖራቸው በመደገፍ ምርቶቹ ወደ ውጪ የሚላኩበትን አሰራር የሚያመቻች ነው ፡፡

እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱት የ3 ሴት ልጆች ብቸኛ አሳዳጊ እናት የሆኑት ወ/ሮ አሰለፈች አበበ አንዷ የዚህ ፕሮጄክት ተጠቃሚ ሲሆኑ በቀድሞ መንግስት በወታደርነት ያገለገሉና በሱዳን ውስጥ ለ5 ዓመት በስደት የኖሩ ናቸው ፡፡ ወ/ሮ አሰለፈች ወደ ኢትዮጵያ ከተመለሱ በኃላ ትዳር መስርተው ልጆች ቢያፈሩም በባለቤታቸው ድንገተኛ ሞት ምክንያት የቤተሰቡ ገቢ እጅግ ቀንሶ ለከፍተኛ ችግር ተዳርገው ነበር ፡፡ ነገር ግን ወ/ሮ አሰለፈች በፕሮጄክቱ ከታቀፉ በኃላ የቤተሰቡ የኑሮ ሁኔታ ተቀይራል።

በዋና ፀሐፊው ጉብኝት ወቅት የድህረ-2015 ዓለም አቀፍ የልማት አጀንዳ አማካሪያቸው ወ/ሮ አሚና መሐመድ አብረው ተገኝተዋል፡፡ ቀዳማዊት እመቤት ወ/ሮ ሮማን ተስፋዬም ፕሮጀክቱን አብረው ጎብኝተዋል፡፡

ይህ ፕሮጄክት በየካቲት ወር 2006 ዓ.ም በእርሳቸው ቢሮ ተመርቆ የተከፈተ ሲሆን ፕሮጄክቱ የሚተዳደረው ሴቶችን ለማብቃትና የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለማድረግ ከተቋቋመው (Center for Accelerating Women Economic Empowerment) እና በኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ማዕከል ((EDC) ነው፡፡ ፕሮጄክቱ 1500 ሴቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው ፡፡

በፕሮጄክቱ የታቀፉት ሴቶች በአብዛኛው ከዚህ በፊት የማገዶ እንጨት በመሰብሰብ እና በመሸጥ ይተዳደሩ የነበረ ሲሆን ገቢያቸውም ከእጅ ወደ አፍ ነበር፡፡ በፕሮጄክቱ ከታቀፉ በኋላ ግን የገቢያቸው ሁኔታ በከፋተኛ ሁኔታ እየተሻሻለ ሲሆን በአማካኝ በአራት እጥፍ አድጓል፡፡

ፕሮጄክቱ በተመረቀበት ወቅት ንግግር ያደረጉት የካናዳ አምባሳደር ዴቪድ አሸር ገበያ የማግኘት ችግር እና የመረጃ እጥረት ትልቁ የሴት ኢንተርፕረነሮች ተግዳሮት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

የካናዳ መንግስት ዋነኛው የኢንተርፕረነርሺፕ የልማት ማዕከል (EDC) አጋር ሲሆን ከ28 ሺህ በላይ ሴቶች የፈጠራ ክህሎታቸውን እና አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ 5.8 ሚሊዬን የአሜሪካ ዶላር እርዳታ ለማዕከሉ አድርጓል ፡፡

## የቢዝነስ ድጋፍ አገልግሎትን ለማሳደግ ስምምነት ተደረገ

የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ማዕከል ከኔዘርላንድ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት (CORDAID) እና (R&D) ተራድኦ ማዕከል ጋር የመግባቢያ ሰነድ ስምምነት ተፈራርሟል ፡፡ ስምምነቱ መካከለኛ ኢንተርፕራይዞችን የቢዝነስ ልማት አገልግሎት ድጋፍ ለማድረግ ነው፡፡ የባለሙያዎች ሴሚናር በነሐሴ 15 ቀን 2007 ዓ.ም ተካሄዷል ፡፡ በስብሰባው ላይ ለተሳታፊዎች በሙያ ላይ የተመሰረተ አሰራር (Professionalism ) እና የቢዝነስ ፈጠራ ግኝቶች ( innovative solutions) የአሰራር የመፍትሔ ሃሳቦች ላይ ውይይት ተደርጓል ::



# የኢንተርፕረነር ስፓርክ

ቅፅ 1 ቁጥር 1 መስከረም 2008

የኢትዮጵያ የኢንተርፕረነርሺፕ ማዕከል ዜና መጽሔት
ቅፅ 1 ቁጥር 1

Entrepreneurship Development Centre (EDC) - Ethiopia
የኢንተርፕሩነርሽፕ ልማት ማዕከል-ኢትዮጵያ

## የሥራ አስፈጻሚዋ መልዕክት



ውድ አንባብያን!

የመጀመሪያውንና በየሩብ ዓመቱ የሚወጣውን የድርጅቱን የዜና መጽሔት ለአንባብያን በማቅረባችን የተሰማኝን ልባዊ ደስታ ለመግለጽ እወዳለሁ ። የተጓዝንባቸው ረዥም መንገዶች፣የስራ ልምዶች፣ እና መልካም ተሞክሮዎች ለኢትዮጵያውያን የስራ ፈጣሪዎች መነቃቂያ ነበሩ ።

የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ማዕከል አትዮጵያ (EDC) እ.አ.አ በ2013 ግንቦት ወር ተመሰረተ። ማዕከሉ በዚያው ዓመት በየካቲት ወር በክቡር ጠ/ሚር ሃ/ማርያም ደሳለኝ የተመረቀውን የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ፕሮግራም አካሂዷል።

ማዕከላችን ለከተማ ቤቶችና ልማት ኮንስትራክሽን ሚኒስትር እና የፌዴራል አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ ተጠሪ የሆነ ተቋም ሲሆን ማዕከሉ የውስጥ አስተዳደር ስልጣን አለው ። ማዕከሉ ኢንተርፕረነርሺፕ ስልጠና እና ራስን ማስቻያ የቢዝነስ ልማት ምክር አገልግሎቶችን በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ አዲስ እና ነባር ጥቃቅን ፣አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች ይሰጣል።

ማዕከሉ ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ በርካታ የፈጠራ ስራ ክህሎት እና ህልም ያላቸውን ወጣት ኢትዮጵያውያንን በመደገፍ ዘለቄታ ያለው ለውጥ እንዲመጣ የራሱን ድርሻ አበርክቷል። በዚህም ሂደት ለስራ አብቅቷል ።ይህንን አገልግሎት የሚያከናውነው እድገትን መሰረት ያደረጉ ኢንተርፕራይዞችን፣ አቅም ያላቸው የስራ ፈጣሪዎችን እና የስራ አጥነትን ለመቅረፍ የሚንቀሳቀሱ ወጣቶችን ደግፎ በገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በማስቻል ነው ።

ባለፉት ሁለት ዓመታት ማዕከሉ ከ5000 በላይ ለሚሆኑ ነባርና ጀማሪ ድርጅቶች የቢዝነስ ድጋፍ እና የምክር አገልግሎት ሰጥቷል።

በተጨማሪም ከ23 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሠልጣኞች የኢንተርፕረነርሺፕ ስልጠና ሰጥቷል ። እንዲሁም ሴቶችንና ወጣቶችን ማዕከል ያደረገ ልዩ ስልጠና በተሳካ ሁኔታ አከናውኗል።

ማዕከሉ ከተለያዩ የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመሆን የኢንተርፕረነርሺፕ ክህሎት ማዕከሎችን (Centers for Excellence) በማቋቋም ላይ ይገኛል። ይኸውም ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀው የሚወጡ ተመራቂዎች ስራ ፈጣሪ እንጂ ሥራ ጠባቂ እንዳይሆኑ ይረዳል። የቅርብ ጊዜ መረጃ እንደሚያመለክተው የከተማ ወጣት ስራ አጦች ቁጥር 22.8 በመቶ ሲሆን የከተማ ሴት ወጣቶች ስራ አጥ ቁጥር 28.8 በመቶ ነው። እነዚህ ማዕከላት በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ፣ በባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣ በአዳማ ዩኒቨርሲቲ እና በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ በመቋቋም ላይ ናቸው ። ከዚህም በተጨማሪ ማዕከላችን ከትምህርት ሚኒስተር የትምህርት ጥናትና ምርምር ማዕከል (Education Strategic Center) ጋር በመሆን የኢንተርፕረነርሺፕ ስርዓተ-ትምህርት እንዲጠናከር እና በዚሁ ረገድ ለፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ጥናትና ምርምሮች እንዲካሄዱ ያግዛል።

ማዕከላችን የስራ አድማሱን በማስፋት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የክልል ቅርንጫፍ ቢሮዎችን በባህርዳር፣ በመቀሌ፣ በሀዋሳ እና በቢሾፍቱ ከፍቶ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል ።

## በዚህ ዕትም:

ርዕሰ ዜናዎች


- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ የሴቶችን የኢንተርፕረነርሺፕ ፕሮጀክት ጎበኙ
- የቢዝነስ ድጋፍ አገልግሎትን ለማሳደግ ስምምነት ተደረገ
- የኢንተርፕረነርሺፕ ስልጠና ሺዎች ተጠቃሚ እያደረገ ነው
- ወጣት የስራ ፈጣሪዎች የራስ ቢዝነስ ግንባታ (BYB) ስልጠና አገኙ
- የኢንተርፕረነርሺፕ አሰልጣኞች በተባበሩት መንግስታት የንግድና የልማት ድርጅት እውቅና አገኙ
- የቢዝነስ ልማት አገልግሎት አማካሪዎች ቁጥር አደገ
- የዓለም ዓቀፍ ኔትወርክ የማህበራዊ ግንኙነት ትብብር (INSHID) የኢትዮጵያ ቅርንጫፍ በይፋ ተከፈተ
- የላቁ ኢትየጵያውያን ኢንተርፕረነሮች ሽልማት ተሰጣቸው
- የመንግስት ከፍተኛ ሀላፊዎች ኢንትራፕረነርሽፕ ስልጠና ወሰዱ
- የፈጠራ ግኝት ማዕከል ተቋቋመ
- በስርዓተ ጾታ ላይ ያተኮረ ስልጠና ተካሄደ
- ቀጣይ ክንውኖች


እ.አ.አ በየካቲት ወር 2013 ጠ/ሚር ሃ/ማርያም ደሳለኝ በተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) እና በከተማ ቤቶችና ልማት ኮንስትራክሽን በጋራ የተጀመረውን የኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ፕሮግራም መርቀው ከፍተዋል። ይህም ፕሮግራም በኢንተርፕረነርሺፕ ልማት ማዕከል አትዮጵያ (EDC) እና በፌዴራል አነስተኛና ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ ልማት ኤጀንሲ ይተገበራል።